በ2013 በጀት ዓመት የተከናወነ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና 267/2011 መሠረት በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለመደበኛ ተግባራትና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን፤ የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው ሕግ፣ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን፣ ከምዝበራና ብክነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የክልሉን የቆዳ ስፋት፣ የአወቃቀር እርከንና የሴክተር አደረጃጀት፣ለየመ/ቤቱ እንዲሁም ለመ/ቤታችን የተመደበውን በጀት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመከተል ያከናወናቸውን ተግባራት ያካተተ ሪፖርት እንደሚያቀርብ ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሠረት መ/ቤቱ ከጥር 1/2012 እስከ ግንቦት 30/2013 ዓ.ም ያከናወነው የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶችን የያዘ ሪፖርት ለምክርቤት አቅርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት የተካተተው የ301 መ/ቤቶች የ2012 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ሪፖርት ውጤት ሲሆን ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሰብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኀላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኦዲት የማስደረግና የሰሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡

1.2 የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የሚገኙበት መንግስታዊ የአወቃቀር እርከን በተመለከተ፡-

የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 301 መ/ቤቶች መካከል በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል ደረጃ የሚገኙ/የማዕከል ተጠሪ የሆኑ 102(34%) ፣ በዞን 11(4%) ፤ በከተማ አስተዳደሮች 75(25%) ቀሪዎቹ 113(37%) የሚሆኑት በወረዳ ደረጃ የሚገኙ ናቸው፡፡

1.3 ለኦዲቱ ጥቅም ላይ የዋለ የኦዲት ስልት በተመለከተ፡-

- የኦዲት ስልት አጠቃቀምን በተመለከተ በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 301 መ/ቤቶች ውስጥ 227(75.42%) የሚሆኑት በናሙና የተሰሩ ሲሆን 74(24.58%) የሚሆኑት መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ በመቅረቡ በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

1.4 የኦዲት አስተያየትን በተመለከተ፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገ 301 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 218 ናቸው። የመጀመሪያ ኢንትሪም ሂሳብ ኦዲት ስራ ብቻ የተጠናቀቀ በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጣቸው 9 መ/ቤቶች ሲሆኑ 74(25%) መ/ቤቶች ደግሞ የልዩ ኦዲት ስራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት መስጠት የማይጠበቅባቸው ናቸው። የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲታይ ለ157 (52%) ከዚህ በስተቀር ፤ ለ25(4%)አጥጋቢ አይደለም እና ለ36(12%) ንፁህ የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል። የኦዲት አስተያየቱ ከ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው"** (በ106%) መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ እና የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያሳይ ሲሆን፣ **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** ከ2 ወደ ምንም መ/ቤት (በ100%) መቀነሱ የኦዲት ማስረጃዎች አቅርቦት ገደብ እየቀነሰ መምጣቱን የሚያመላክት ነው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል " **አጥጋሚ አይደለም የሚለው"** ከ10 ወደ 25 (በ250%) መጨመሩ የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ ድክመት፣ማጭበርበር እና በሪፖርት አቀራረብ ላይ ያሉ ጉልህ መዛባቶች እየጨመሩ መምጣታቸውን ያመላክታል። የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ ከ39 ወደ 74 መ/ቤት (በ89.74%) መጨመሩ ህብረተሰቡ ብልሹ አሰራሮችን የመታገል ልምዱ እና ስጋተ ኦዲትን መሰረት አድርጎ የኦዲት ስራን የመፈፀም ትኩረት እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ያመላክታል። መንግስት የመደበላቸውን ሀብት/ገንዘብ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ፣አብክመ ንግድና ገቢያ ልማት ቢሮ፣አማራ ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽ/ቤት ፣ ቡሬ ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ፣ አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ወልዲያ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ፣ ሃብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ አምሃራ ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ወረኢሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ደቡብ ወሎ ዞን ገንዘብ መምሪያ ፤ ለገሂዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ መሃል ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ አርጡማ ፋርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ሃገረ ማሪያም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ፣ መንዝ ቀያ ገብርኤል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ፣ ሸዋ ሮቢት ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ፣ ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል እና አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ናቸው።

1.5 የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ፡-

- በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 227 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 74(32.60%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ይህም የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡ በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 74 መ/ቤቶች ውስጥ ደግሞ እርምጃ ያልተወሰደባቸው 40(54.05%) እና በፖሊስ ምርመራ እና በክስ ሂደት ላይ ያሉ 34(45.95%) መ/ቤቶች በመሆናቸው እርምጃ የመውሰድ ሂደቱ አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ለኦዲት ግኝቶች የእርምት አወሳሰድ ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ናቸው፡፡

ክልል/ማዕከል ተጠሪ መ/ቤቶች

1. ራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት
2. ሃብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት
3. ወልድያ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
4. ወልዲያ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
5. ሐይቅ ከተማ አስተዳደር ማረሚያ ቤት
6. ሐይቅ ማረሚያ ቤት-2011 በጀት ዓመት
7. ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
8. አብክመ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ
9. አማራ ክልል ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፍሳሽ አገልግሎት አሰሪዎች ማህበር
10. አብክመ ማረሚያ ቤቶች ከሚሽን
11. ባህር ዳር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
12. አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
13. ዳንግላ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል
14. ደቡብ አቸፈር ወረዳ ፍ/ቤት
15. ደቡብ ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ
16. አለፋ ወረዳ ፍ/ቤት
17. አማኑኤል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ
18. ይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍ/ቤት

ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር

19. ባህርዳ ከተማ አስ/ገቢዎች መምሪያ

ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር

20. ሰሜን ሜጫ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ማዕከል
21. ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ማዕከል
22. ፍኖተ ሰላም ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
23. መራዓዊ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
24. ፍኖተ ሰላም ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
25. ቡሬ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት

ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር

26. ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ማዕከል
27. ደብረ ማርቆስ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
28. አነደድ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ማዕከል

ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር

29. አለፋ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ሰ/ማዕከል

ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር

30.ሰሜን ጎንደር ዞን ነ/ፋ.ይ/ድ/ማዕከል

ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

31.ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ.ይ/ድ/ሰ/ማዕከል

32.ጉና በጌምደር ወረዳ ነ/ፋ.ይ/ድ/ሰ/ማዕከል

አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር

33.አዲስ ቅዳም ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

34.መቅደላ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

35.አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

36.ደላንታ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

37.ከላላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

38.ኩታበር ወረደ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

39.ወረኢሉ ወረደ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

40.ቦረና ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

41.ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

42.ወረባቦ ወረደ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

43.አማራ ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

44.ተንታ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

45.መሃል ሳንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

46.ሀይቅ ከተማ አስተዳደር ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር

47.ጅሌ ጡሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

48.ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

49.ዳዋ ጫፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

50. ምንጃር ሸኮራ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

51. መንዝ ጌራ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

52. መንዝ ማማ ምድር ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

53. እንሳሮ ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

54. ሞጃና ወደራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

55. መርሀ ቤቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

56. ሸዋ ሮቢት ከተማ አስ/ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

57. ሚዳ ኦሮሞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

58. አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

59. መንዝ ቀያ ገብርኤል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

60. ሞረትና ጅሩ ወረደ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

61. አንኮበር ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር

62.ላሊበላ ከተማ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

63. ወልድያ ከተማ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

64.ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

65.ቡግና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

66.ቆቦ ከተማ አስ/ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

67.መቄት ወረዳ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

68.መርሳ ከተማ አስ/ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

69.አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

70.ወልድያ ከተማ ገቢ.ዎች ጽ/ቤት

ዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር

71. ዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን
ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
72. ዝቃላ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት
73. ጋዝጊብላ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት
74. ሰቆጣ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

1.6. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

1.6.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 8,981,215.66 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 6,626,874.62 ከቀድሞ ገንዘብ ያዦች የተገኘ ጉድለት ነው፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ/30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ10 መ/ቤቶች ብር 3,504,098.41 የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ7 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 10,782,121.14 ተስተውሏል፡፡ ዝርዝሩን (በዝገባ ሪፖርቱ አባሪ 2ን ይመልከቱ፡፡)

1.6.2 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች፡-

- አንጎት ወረዳ ገንዘብ ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ24/04/2010-30/10/2012 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,361,897.04፣
- የጥምረት ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር የማህበሩ የንብረትና የሽያጭ ሰራተኛ የሆኑት ከ11/06/2003 ዓ/ም እስከ 1204/2005 ዓ/ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,259,062.99፣
- ደቡብ አቸፈር ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የግዥ ሰራተኛ የሆኑት ከ01/5/2009-09/01/2010 ዓ.ም ያቀሳቀሱት የተሰብሳቢ ሂሳብ እና ረዳት ገንዘብ ያዥ

ሁነው በሰሩበት ከ10/01/2010-28/09/2012 ዓ/ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የገቢ እና ወጪ ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 991,141.74፣

- ባህር ዳር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ የነበሩት ከ12/12/2006 ዓ/ም እስከ 25/03/2012 ዓ/ም ድረስ ያልቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 731,830.48፣
- ሹምአቦ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ዋና ገንዘብ ያዥ ከ01/11/2010-30/10/2011 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 685,152.33 እና በግዥና ፍይናንስ ንብረት አስተዳደር አስተባባሪ ስም በአደራ ከእለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ተሰብስቦ ለተቋሙ ፈሰስ ሳይደረግ የቀረ ጥሬ ገንዘብ ብር 10,884.85 በድምሩ ብር 696,037.18፣
- የከለላ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ግዥ ኦፊሰር የነበሩት ከ1/11/20007-30/8/2011 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 365,673.07፣
- ቅዳማጃ ንፅስ መዘጋጃ ቤት ገንዘብ ያዥ ከ09/10/2008-24/08/2009 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 359,781.57፣
- የሳላ ሰየምት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የግዥ ባለሙያ የነበሩት ከ2006-2008 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 70,853.15 ፣ የግዥ ባለሙያ የነበሩት ከ2004-2008 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 153,356.67፣የግዥ ባለሙያ የነበሩት ከ01/11/2003-30/10/2008 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 36,031.21 በድምሩ ብር 260,241.03፣
- የለገሂዳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤትረዳት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ18/09/2006-30/5/2012 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 232,880.26፣
- ቡሬ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የግዥ ኦፊሰር የነበሩት ከ18/04/2006-11/01/2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከኮሌጁ በተሰብሳቢነት ያወጡት ገንዘብ ስራ ላይ ማዋላቸው ሲረጋገጥ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 137,115.46፣
- ደቡብ አቸፈር ወረዳ የቃጥ ድኩሊ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ዋና ገንዘብ ያዥ እና የዕቃ ግዥ ሰራተኛ ከ01/11/2009-15/5/2011 ዓ.ም ያቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 108,848.41፣

- ደብረ ኤልያስ ወረዳ የጎፍጭማ ቀበሌ አስተዳር ጽ/ቤት ገንዘብ ያዥ ከ29/1/2004-30/2/2009 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 93,697.10፣
- በአንጎት ወረዳ አሁን ተገኝ እና እሸት አምባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተገኘ ጉድለት በተመለከተ፡- በአሁን ተገኝ 2ኛ/ደረጃ ት/ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ15/04/2005-21/10/2009 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 35,390.51 ፣ በእሸት አምባ 2ኛ/ደረጃ ት/ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ29/03/2008-15/10/2010 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 53,248.80 በድምሩ ብር 88,639.31፣
- የመካነ ኢየሱስ ከተማ አስተዳደር ንግድ ገበያ ልማት ጽ/ቤት ከንግድ ምዝገባ ፈቃድ ገቢ ከ23/02/2010 እስከ 09/9/2011 ዓ.ም የተሰበሰበ የገቢ እና ፈሰስ ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 61,568.00፣
- የአቦ ሜዳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢና ካርድ ክፍል የነበሩት ከ21/8/2005-19/3/2007 ዓ/ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኝ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 54,660.58፣
- ሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የቀራኒዮ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለት እጅ እነሴ ወረዳ የቡሀ-ገልጥ ቀበሌ ሊቀመንበር የነበሩት ከ12/06/2010 እስከ 29/8/2010 ዓ.ም ለትምህርት ቤት ማሰሪያ ከማህበረሰቡ የሰበሰቡት ገቢ እና ወጪ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 34,450.00፣ የሁለት እጅ እነሴ ወረዳ የደብረ-ሰላም ቀበሌ ሊቀመንበር የነበሩት ከ26/5/2010-26/6/2011 ዓ.ም ለትምህርት ቤት ማሰሪያ ከማህበረሰቡ የሰበሰቡት ገቢ እና ወጪ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 9,300.00፣የሁለት እጅ እነሴ ወረዳ የየሽጌ-ቀራኒዮ ሊቀመንበር የነበሩት ከ2/5/2011-25/6/2011 ዓ.ም ለትምህርት ቤት ማሰሪያ ከማህበረሰቡ የሰበሰቡት ገቢ እና ወጪ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 3,050.00 በድምሩ ብር 46,800.00፣
- የወረባቦ ወረዳ የቢስትማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የግዥ ባለሙያ ከ01/11/2011 እስከ 30/10/2012 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 29,943.50፣
- ቡሬ ዙሬያ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ረዳት ገንዘብ ያዥ ከጥር 1/2011 እስከ መስከረም 30/2012 ዓ/ም የተለያዩ ክፍያዎች ከባንክ በተሰብሳቢ ሂሳብ ወጪ አድረገው ለተለያዩ ወጪዎች የፈፀሙት ክፍያ ኦዲት ሲደረግ የተገኘ ጉድለት ብር 13,943.30 እና ረዳት ገንዘብ ያዥ ከጥር 1/2011 እስከ መስከረም 30/2012 ዓ/ም

የተለያዩ ክፍያዎችን ከባንክ በተሰብሳቢ ሂሳብ ወጪ አድርገው ለተለያዩ ወጪዎች የፈፀሙት ክፍያ ኦዲት ሲደረግ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 6,807.07 በድምሩ ብር 20,750.37 ነው፡፡

- በደሴ ዙሪያ ወረዳ የጌልሻ መሪ መዘጋጃ ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ27/05/2009-15/8/2011 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 25,522.10፣
- በዋና ኦዲተር መ/ቤት የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ25/12/2009-04/13/2011 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 18,142.14፣
- የወግዲ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ18/04/2010-08/9/2010 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 15,067.74፣
- ➢ በከለላ ወረዳ የከለላ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ26/03/2010-1/13/2011 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 14,303.73፣ ከ10 ሺህ ብር በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

በመሆኑም ከገንዘብ ያዦች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት በፖሊስ ምርመራ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 1,132,398.79፣ በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ ብር 4,447,186.42 እንደሚገኝ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 3,401,630.45 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

1.6.3 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች:-

- ➢ የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 227 መ/ቤቶች ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው 24(10.57%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ (ዝርዝራቸው በዋናው ዘገባ ሪፖርት ተመልክቷል፡)

1.7. የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

1.7.1 የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፡-*

- ➢ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ5 መ/ቤቶች ብር 2,348,398.76 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
- ባህር ዳር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 1,774,806.76 ፤ቪዥን የእናቶች ጤና ድርጅት ከጤና ጣቢያው ጋር ባለው የዱቤ ህክምና ስምምነት መሰረት የተጠቀመበትን የምርመራ

እና የመድሀኒት ክፍያ ሲፈፀም ከድርጅቱ በእለት ገንዘብ ሰብሳቢው ተሰብስቦ ለጤና ጣቢያው ገቢ እንዲሆን ከተላከው ገንዘብ ውስጥ ለከፋይ ከሚሰጠው በራሪ የገቢ ደረሰኝ ቅጠል ላይ ትክክለኛውን ገንዘብ መጠን በመፃፍ ነገር ግን በኮፒው (በቀሪው) ደረሰኝ ቅጠሎች ላይ እያሳነሱ ገቢ በማድረግ በማጭበርበር ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ እና ቪዥን የእናቶች ጤና ድርጅት (ቪዥን ማተርኒቲ ኬር) ለዱቤ ለታከሙ ህሙማን ወደ ጤና ጣቢያው ገቢ እንዲሆን በቼክ ለእለት ገንዘብ ሰብሳቢው የላከው ሂሳብ ለጤና ጣቢያው ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ የሌለው እና ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣

- አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 500,565.00 በተያዘው ውል ስምምነት አቅራቢ ድርጅቱ ማቅረብ የነበረበት ብዛት 193 ላፕቶፕ ኮምፒተሮች ሲሆኑ ነገር ግን ብዛት 118 ላፕቶፕ ኮፒውተር ብቻ ያቀረበ በመሆኑ በውል ስምምነቱ መሰረት በውድድር ያሸነፈውን ብዛት ላፕቶፕ ባለማቅረቡ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ የውል መስከበሪያ ሂሳብ፣
- በዋና ኦዲተር መ/ቤት የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 26,211.00 ከመለዋወጫ አቅራቢ ድርጅቶች የውል ማስከበሪያ የተሰበሰበ እና የተሰበሰበበትን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቅጠል ቮይድ/የተበላሸ በማለት በማጭበርብር ለግል ጥቅም የዋላ ሂሳብ፣
- የአማራ ህዝቦች ሰማታት መታሰቢያ ሀውልት ጽ/ቤት ብር 25,248.00 ያለገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በዋና ገንዘብ ያዥ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ እና በጠፋ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ፣
- ወልድያ ከተማ አስተዳደር ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ብር 21,570.00 የ04 ቀጠና የጁ ገነት ጎጥ ገንዘብ ሰብሳቢ የሆኑት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ወጭ ባደረጉት የተሰበሰበ ገንዘብ የጤና መድህኑን ሲያስተባብሩ ለነበሩት ግለሰብ ፈሰስ እንዲያደርግ ተሰጥቶ ገቢ ሳይሆን ለግል ጥቅም የዋለ የገቢ ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 21,570.00 በፍርድ ቤት የክስ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ቀሪው ብር 2,326,828.76 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

1.7.2 ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፡-

- የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበትና

ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ2 መ/ቤቶች ብር 463,583.59 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይደረግ ክፍያ የተፈፀመባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰጭ/ማዕከል ብር 445,311.56** የአንቦ ሜዳ ሻሞ መንገድ ግንባታ 3ኛ ዙር፣የአንቦ ሜዳ እስትንፋስ መንገድ ግንባታ 4ኛ ዙር ክፍያ ለስራ ተቋራጩ ሲፈፅም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- **ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 18,272.03** ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ለደብረ ሞይ ቀበሌ የውሃ ግንባታ 1ኛ እና 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ተቋራጮች ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ አልደረሰንም፡፡

1.7.3 ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ በተመለከተ፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገ 301 መ/ቤቶች ውስጥ በ107 መ/ቤቶች ብር 295,183,360.47 ባለው የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መሰረት ገቢ በወቅቱ ሳይሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግስት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ብር 82,894,648.99(28%) ፣ ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ብር 50,220,859.25(17%) ፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር ብር 42,135,574.18 (14%) ፣ ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ብር 41,419,625.10(14%) እና ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር 37,803,166.89 (13%) ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው እንደሚገኙ ሪፖርቱ ያመላክታል::
- መንግስት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል:: ስለሆነም ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ በ2 መ/ቤቶች ብር 284,244.00 (0.09%) ስለመሰብሰቡ በግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው

ብር 294,899,116.47 እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 23/2013 ዓ/ም ድረስ ስለመሰብሰቡ አልተገለፀም፡፡

1.7.4 ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፡-

- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ43(14.29%) መ/ቤቶች ብር 298,798,705.02 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 263,947,874.23 የያዙ 504.82 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ወግዲ ወረዳ ነ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 5,696,507.10 የያዙ 75 ጥራዝ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 4,892,380.85 የያዙ የመደበኛኛ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ሀብሩ ወረዳ ነ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 4,467,586.05 የያዙ 10.38 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ደቡብ አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 4,004,885.35 የያዙ 62 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኞች ፣ 28.2 ጥራዝ የግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣መርሳ ከተማ አስ/ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,410,897.95 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 1,828,414.66 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ሰቆጣ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 1,678,805.28 የያዙ 136.25 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,294,246.74 ያያዙ 48.69 ጥራዝ የመደበኛ እና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ሞጃና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,267,480.00 የያዙ 236.4 ጥራዝ የእርሻ ስራ ገቢ ግብርና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ጉባላፍቶ ወረዳ ወረዳ ነ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,235,736.33 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,105,263.00 የያዙ የእርሻ ስራ ገቢ እና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ ከብር 1,000,000.00 በላይ የያዙ ደረሰኞች ለኦዲት ባለማቅረብ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

- ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሁን አይሁን ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ካልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ዉስጥ ብር 59,272.50 (0.02%) የያዙ ገቢ ደረሰኞች ብቻ ቀርበው በውስጥ ኦዲት

የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 298,739,432.52 ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ ወይም ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 23/2013 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

1.8.የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

1.8.1 በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ115 መ/ቤቶች ብር 3,939,749,122.20 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ተሰብሳቢ ሂሳብ ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡
- ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም ከመዝገብ የመሰረዣ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል-4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡ ሆኖም ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 56,846,119.88(1.44%) ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 3,882,903,002.32 ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡ በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ከሚሰበሰብባቸው አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ16 መ/ቤቶች ብር 65,591,055.76 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

1.8.2 ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ32 መ/ቤቶች ብር 84,501,064.06 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ከመዝገብ ለመሰረዝ የማያስችል በመሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በየስሙ ተለይቶ የተቀፅላ

ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ስለመኖሩ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመቅረቡ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

1.9 የወጪ ሂሳብ ኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

1.9.1. *የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፡-*

➢ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ21 መ/ቤቶች ብር 11,118,146.21 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና የአፈፃፀም ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **የአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ቻናል-2 ሂሳብ** ብር 2,973,208.33 በ2007/2008 በጀት ዓመት ግንባታቸው ተጀምሮ የተቋረጠው የሰቆጣ ደም ባንክ ግንባታ በአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ መ/ቤት በድርድር የተዘጋ ቢሆን ከስራ ተቋራጩ ሳይሰበሰብ የቀረ ቅድሚያ ክፍያ ፣የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ እና ከማዘግየት ቅጣት ከስራ ተቋራጭ ሳይሰበሰብ የቀረበ ሂሳብ ብር 2,298,830.72 ፣ መስክ ሳይወጣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 15,300.00 ፣ በጉባላፍቱ ወረዳ የሳንቃ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የእድሳት ግንባታ ፣ የካላዛር የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ግንባታ ፣ በጃቢ ጠህናን ወረዳ የፈተገም ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፣ በጃናሞራ ወረዳ የአሰንጋ ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፣ በባንጃ ወረዳ ከሳ ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፣ እንዳቤት ወረዳ በጎኖ ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፣ በጃቢ ጠህናን ወረዳ የፈተገም ጤና ጣቢያ ህንፃ ግንባታ እና በሰከላ ወረዳ የአጉት ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ ለማከናወን ተቋራጮች በውል ስምምነቱ መሰረት ለመፈፀም ባለመቻላቸው የግንባታ ማቋረጫ ሰነድ ተዘጋጅቶ ተቋራጮች ስራ ሳይሰሩ በብልጫ የተፈፀመ ክፍያ ብር 332,308.97 ፣ የመተማ ካላዛር ሆስፒታል ህንፃ ግንባታ ፣ የደብረ ኢየሱስ ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፣ የጣዕመ ጤና ጣቢያ ህንፃ ግንባታ ፣ በጃቢ ጠህናን ወረዳ የፈተገም ጤና ጣቢያ ህንፃ ግንባታ እና በሳይንት ወረዳ የአዋ ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ስራ ለማከናወን የውል ስምምነት የፈፀሙት የስራ ተቋራጮች በውል ስምምነቱ መሰረት ስራውን መጨረስ ባለመቻላቸው የግንባታ ማቋረጫ ሰነድ በሚዘጋጅበት ወቅት ለቀጣዩ አዲስ የስራ ተቋራጭ ስራው እንደሚሰራ በውል ስምምነት ተጨምሮ የውል ስምምነት የተገባ ቢሆንም ነገር ግን ሂሳቡ ከቀድሞው የስራ ተቋራጭ መሰብሰብ ሲኖርበት ሳይሰበሰብ የተገኘ ብር 312,603.86 እና በሁለት እጅ እነብሴ ወረዳ የየጭቃ ጤና ጣቢያ ፣ በሳይት

ወረዳ የኮተት ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ የግንባታ የስራ ተቋራጮች በውል ስምምነቱ መሰረት ስራቸውን መፈፀም ባለመቻላቸው የግንባታ ማቋረጫ ሰነድ ሲዘጋጅ በብልጫ የተገኘ ሂሳብ ብር 14,164.78፣

- **ኮምቦልቻ ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት ብር** 2,932,044.23 የመኖሀሪያ ማሳደግ ግንባታ ስራ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም ከውል ዋጋ በላይ የተፈፀመ፣
- **አዲስ ቅዳም መሪ መዘጋጃ ቤት ብር** 2,569,618.46 በከተማው በ2010 በጀት ዓመት ተጀምረው ለተከናወኑ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጠጠር ማልበስ ስራ ላከናወኑ የስራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸም ከተሰራው ስራ በላይ አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 2,224,841.22፣ በከተማው በተለያዩ ቦታዎች የዲች ቦይ ግንባታ ሲከናወን ላልተሰራ የዲሽ ቦይ ግንባታ ስራ በብልጫ ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ ብር 245,278.20፣ በ2009 በጀት ዓመት ለ2-የካልበርት ግንባታ ስራ ላከናወነ የስራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 3,010.00 ፣ በ2010 በጀት ዓመት ላልተሰራ የኮበል እስቶን ግንባታ ስራ ለስራ ተቋራጭ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 96,489.04፣
- **ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ደም ባንክ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር** 610,327.19 የኮቪድ አገልግሎት ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ መጡበት ከተባለበት መ/ቤት ተቀጣሪ ላልሆኑ ወይም ለማይታወቁ እና በኮቪድ ስራ ላይ ላልተሳተፉ ሰራተኞች የተከፈለ እንዲሁም የአዳር ስራ ላልሰሩ ሰራተኞች የተከፈለ የተረኝነት አበል፣
- **የአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር** 364,000.00 በውይይቱ ላይ ተሳትፈዋል የተባሉ ጠማርያን እነማን እንደሆኑ በስም እና ብዛታቸው ባልታወቀበት ሁኔታ፣ክፍያው ለተሳታፊዎች በቀጥታ መከፈል ሲገባው ለባርኮን ቱሪዝም ማስታወቂያና ኩነት ዝግጅት ለተሳታፊዎች ይከፍላል በሚል ምንም ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የተከፈለ እና ስልጠናውን የተሳተፉ አካላት በስልጠናው ለመሳተፋቸው ምንም ማስረጃ በሌለበት ደረጃ የተከፈለ ክፍያ፣
- **የመርከብ ሁለገብ ገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየን ብር** 198,478.00 መርከብ ዩኒዮን ከአብክመ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ በወሰደው ውክልና መሰረት በደቡብ አቸፈር ወረዳ ለሚገኘው የቀልጣፋ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር አገልግሎት የሚውል መጋዝን ግንባታ ለአከናወነው ተቋራጭ የ2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም እና በደብረ ኤልያስ ወረዳ ለሚገነባው የጓይ መጋዝን ግንባታ ለአከናወነው የስራ ተቋራጭ የ2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በውሉ ስምምነት የተገባውን የነጠላ ዋጋ አስተካክሎ ከፍ በማድረግ ከውለታ በላይ በብልጫ የተፈጸመ ክፍያ፣

- **የመህል ሳይንት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 188,954.80 የወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት በ2010 በጀት ዓመት በወረዳው አህዩ 039 ቀበሌ አነስተኛ ግድብ ግንባታ ለማከናወን ከውሃ ስራዎች ተቋራጭ ማህበር ጋር በወሰዱት የስራ ውል መሰረት ስራው ሳይሰራ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **የአብክመ አመራር አካዳሚ ብር** 171,372.00 መለዋወጫ እቃዎች ከንብረት ክፍል ወጥተው እና በኩፖን ነዳጅና ቅባት ተገዝቶ ወጪ ተደርጎ ለጋራዥ የተሰጠ ቢሆንም ለተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ሳይውል የተገኘ፣ላልተገጠመ ዕቃ የተሰራበት ተብሎ ለእጅ ዋጋ የተከፈለ እና ስራዎች አስቀድሞ ውለታ ሳይያዝላቸው ወይም ሳይሰሩ ለጋራዥ ባለሀብቱ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **እንጅባራ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 165,759.58 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሳይያዝ ቅድሚያ ክፍያ ተሰጥቶ አሸናፊው ግለሰብ የመንገድ መብራት አገልግሎት ጥገና ስራ ሳያከናውን ከአካባቢው በመጥፋቱ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **ሸንዲ ከተማ የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ብር** 137,692.00 ቦታው ለግንባታ በመፈለጉ ምክንያት ለባለይዞታዎች የካሳ ክፍያ ሲፈፀም ቦታ ላይ ከአለው የቋሚ አትክልት ብዛት በላይ አላግባብ ተገምቶ የተከፈለ የካሳ ክፍያ፣
- **ደቡብ ሜጫ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ብር** 130,851.10 የወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ንብረት የሆነችው ተሽከርካሪ ለጥገና ጋራዥ በነበረችበት ወቅት አላግባብ የስራ ስምሪት ላይ እንዳለች ተደርጎ ነዳጅ እንደተሞላ በማስመሰል ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 13,192.00 ፣ በማይመለከታቸው ኃላፊ ከንብረት ክፍል ወጭ ሆኖ ለግል ጥቅም የዋለ የነዳጅ ሂሳብ ብር 5,758.10 ፣ ከወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት በጀት ስልጠና በተሰጠበት ከተማ ለሚገኙ የጽ/ቤት ሰራተኞች፣መስክ ወጥተው ስራ ላላከናወኑ የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች እና ስልጠና ላይ ላልተሳተፉ ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 111,901.00፣
- **ታች ጋይንት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 123,750.00 በ2004 በጀት ዓመት ለመስከረም እና ጥቅምት ወር ለአዳጋ ተጋላጭ ተረጅዎች መከፈል የሚገባው የሴሰፍቲኔት ሂሳብ ሳይከፈል የተከፈለ በማስመሰል የሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት እና በዱካ በመፈረም ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 117,600.00 እና የቀበሌ ነዋሪ ያልሆኑ ወይም ለማይታወቁ ግለሰቦች የአዳጋ ተጋላጭ ዝርዝር በፔይሮል ውስጥ ስማቸው እንዲካተት በማድረግ አላግባብ የተከፈለ የሴፍቲኔት ሂሳብ ብር 6,150.0፣
- **የለገሂዳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 117,200.78 የለገሂዳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ከጃማ ደለነ እስከ ለገሂዳ ወረዳ ማዳበሪያ ለማጓጓዝ እንዲሁም የለገሂዳ

ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ፣ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ፣ እንስሳት ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች የተለያዩ የግንባታ ቁሳቁሶችን ወደ ተለያዩ ቀበሌሎች ለማጓጓዝ የጭነት መኪና አገልግሎት ግዥ እንዲፈፀም በጠየቁት መሰረት የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የግዥ ኦፊሰሮች በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ አገልግሎት ግዥውን ሲያከናውኑ ሶስት ተጫራቾች እንደተወዳደሩ በማስመሰል የሀሰተኛ ጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት ቀደም ሲል በሌላ የውድድር ሂደት ነጋዴዎች ለዚሁ ጽ/ቤት ያቀረቡትን የንግድ ፈቃድ ኮፒ አድርጎ በማያያዝ በውድድሩ አሸነፈ የተባለው ተወዳዳሪ ቀደም ሲል ውክልና ለሰጠው እና ይህ ውክልና ውድድሩ ተካሂደ ከተባለበተ ቀን በፊት በፍትህ ጽ/ቤት የተሻረን ማስረጃ በማያያዝ እንዲሁም ተሸከርካሪው ለማጓጓዙ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ እና በግዥ ሂደቱ ሁሉም ነጋዴዎች ባልተወዳደሩበት ሁኔታ እንደተወዳደሩ በማስመሰል የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣

- **ጃናሞራ ወረዳ እንስሳት ሀብት ተጠሪ ጽ/ቤት** 114,482.20 በሰኔ ወር ውሎ አበል ሂሳብ በጀት ዝውውር የተደረገ ሲሆን ዝውውር ከመደረጉ በፊት ያሉት በውሎ አበል ያልተሸፈኑ ቀናት እየተመረጡ ለተጠሪ ጽ/ቤት ሰራተኞች እና የበጀት ዝውውሩን ለመፈፀሙ እንዲሁም የክፍያ ሰነድ የማዘጋጀት እና የማፅደቅ ድርሻ ላላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የተለያዩ ሰራተኞች የመስክ ስራ ባልተወጣበት ሁኔታ መስክ እንደወጡ በማስመሰል የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ጎንደር ከተማ አካል ጉዳተኞች ከህሎት ማበልጸጊ ማዕከል ብር** 97,242.81 ላልተሰራ ስራ የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት እና የስራ ዝርዝር በማዘጋጀት አላግባብ የተከፈለ የመሰበሰሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ክፍያ፣
- **የሳይንት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 95,474.14 በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ውስጥ ባሉት ት/ቤቶች ከ01/01/2008-30/12/2009 ዓ.ም ድረስ ያለው የደመወዝ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በለቀቁ አራት መምህራን ስም ወጭ ሆኖ ለገንዘብ ያዥ ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **የአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት ብር** 56,680.00 መስክ ተወጥቶ ሳይሰራ በመደበኛ የስራ ቦታ ላይ ለተገኙ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች እንዲሁም በጀት ዓመቱ በመጠናቀቁ የውሎ አበል በጀት በመትረፉ ምክንያት በማኔጅመንት አባላት ተወሰወኖ መስክ ላልተወጣ ስራ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 48,490.10 እና ተሸከርካሪውን ለመንግስት ስራ እንዲንቀሳቀስ ከተፈቀደለት ቦታ ውጭ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በማንቀሳቀስ አላግባብ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 8,189.90፣

- **የግዳን ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 30,000.00** የግብርና ጽ/ቤት በሴፍቲኔት በጀት ለ015 ቀበሌ የመስኖ ግንባታ ለማከናወን በሚል ስበብ ምንም ዓይነት ውድድር ባልተደረገበት እና ግንባታው ባልተከናወነበት ሁኔታ በግብርና ጽ/ቤት የማኔጅመንት ኮሚቴ ሰርተዋል በሚል ተወስኖ ውለታ እንደተያዘ ተደርጎ ስራው ሳይሰራ የሀሰተኛ የመሀንዲስ ሰነድ በማዘጋጀት፣ገንዘቡ በተለያዩ ግለሰቦች ስም ወጭ በማድረግ ግለሰቦች ገንዘቡን ለአንድ ግለሰብ እንዲሰጡ ተደርጎ ለግለሰብ ጥቅም የዋለ የመንግስ ገንዘብ፣
- **አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት 21,594.59** በኖርማላይዜሽን ከተፈቀደው በላይ በብልጫ ጥቅም ላይ የዋለ የነዳጅ ሂሳብ ብር 17,714.59 እና የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት አንቡላስ ለጥገና አገልግሎት ሞኤንኮ ባህር ዳር ከተማ ጋራዥ ገብታ እያለ ተሸከርካሪው ባልተሰማራበት ሁኔታ ለሹፌሩ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 3,880.00፣
- **ደንቢያ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ብር 13,256.00** ግለሰቡ ወደ ሆስፒታሉ ከመመደባቸው በፊት ማክሰኝት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ እየሰሩ በነበረበት ጊዜ የሆስፒታሉን ስራ እንደሰሩ ተደርጎ ሳይሰሩ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 6,104.00 እና መስክ ሳይወጡ በመደበኛ ስራ ቦታቸው ላይ ሆነው መስክ እንደወጡ በማስመሰል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 7,152.00፣
- **ጃናሞራ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 6,160.00** አላግባብ በተመሳሳይ ቀናት በድጋሚ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ የውሎ አበል ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት በፍርድ ቤት የክስ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 766,159.10፣በፖሊስ ምርመራ ሂደት የሚገኝ ብር 159,286.59 ሲሆን ቀሪው ብር 10,192,700.52 በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልተገለፀልንም፡፡

1.10. ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተመለከተ፣

- በ11 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,379,361.49 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡
- ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ (ስራ ተቋራጮች) እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው

የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በትኩረት ሊሰራ ይገባዋል፡፡

1.11. አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ፤

- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ106(35.2%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 12,443,844.63 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 150,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ-2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር** 3,032,391.36 ፍኖተ ሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል እስከ 6ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በድምር ስህተት በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣በባህር ዳር ከተማ የተቀናጀ የማህበረሰብ ተኮር የጨቅላ ህፃናት ጤና አገልግሎት ስልጣና ተሰጥቶ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የፀደቀ የስልጠና አበል እና የደንበጫ ጤና ጣቢያ ሪኖቬሽን የተገነባበት የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም ከውል በላይ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **ደብረ ታቦር ከተማ አስተዳር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,692,026.66 ከእናቲቱ ማርያም 1ኛ ደረጃ ት/ቤት እስከ ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን የመንገድ ስራ ለተከናወነበት የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተፈፀመ ክፍያ፣
- **ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 535,583.32 በወረዳው ውስጥ በተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች የውሎ አበል ክፍያ ሲፈፀም መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ፣ቀበሌ መስክ ለወጡበት ውሎ አበል ሲከፈል ከታሪፉ በላይ ፣በድጋሜ የተከፈለ የውሎ አበል እና የባቲ ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ መድሀኒት አቅርቦት ኤጀንሲ በ2009 ዓ/ም መድሀኒት ግዥ ተፈጽሞ የፀደቀን ሂሳብ በ2012 በጀት ዓመት ማስረጃዎችን በማያያዝ በድጋሜ የተፈፀመ ክፍያ የተፈጸመ፣
- **ወረኢሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 485,169.00 መስክ ሳይወጣ ቢሮ ውስጥ ተሁኖ እና መስክ እንደወጡ ተደረጎ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣ በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣ለትምህርት ለሄደ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ አላግባብ የተከፈለ የወንበር አበል፣
- **ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 399,000 ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ ፣መስክ ለስራ ሳይወጡና መስክ ከወጡበት ቀን በላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ-2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር** 363,561.21 ጤና ቢሮው በግሸ አባይ ጤና ጣቢያ የእናቶች ማቆያ እና የባለሙያዎች ግንባታ ለሚያስገነባው 2ኛ ዙር፣የደብረ ማርቆስ ጠቅላላ ሆስፒታል 4ኛ ዙር ፣በቋሪት ወረዳ ለእናቶች ህፃናት ግንባታ 2ኛ ዙር ፣በደሴ

ዙሪያ ወረዳ ጤና ጣቢያ የእናቶች ህንፃ ግንባታ 2ኛ ዙር ፣በደቡብ ጎንደር ዞን በጉራምባ ጤና ጣቢያ የቀዶ ጥገና ግንባታ የመጨረሻ ዙር ፣በቡሬ ዙሪያ ወረዳ ቡሬ ባጉና የፀበል ቦታ ውስጥ ባለ24 መቀመጫ መፀዳጃ ቤት የ1ኛ እና 2ኛ ዙር ፣በበለሳ ወረዳ ባርባፀጓር ጤና ጣቢያ ውስጥ ለሚያስገነባው የጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ 2ኛ ዙር ፣በጎንደር ዙሪያ ወረዳ የአምቦ በር ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ የ3ኛ ዙር ፣በደሴ ዙሪያ ወረዳ አስግዶ ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ የመጨረሻ ዙር፣በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ በመኮይ ጤና ጣቢያ ውስጥ ለሚያስገነባው የቀዶ ጥገና ህንፃ የ1ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣በተመሳሳ ቀናት በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል እና ስልጠና ላልተሳተፉ ሰራተኞች የተከፈለ የስልጠና አበል እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ብርሀን ከተማ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ ለሚያስገነባው የስኪል ላብ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከውል በላይ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣

- **መርሳ ከተማ አስ/ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 349,092.99 መርሳ ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽ ጽ/ቤት ላሰረው የአደጋ ግዜ መውጫ ደረጃ ግንባታ ስራ ዝቅተኛ ተጫራጭ ቀርቦ ሳለ ያለምንም አሳማኝ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ከአቅረበው አቅራቢ የተፈፀመ የግንባታ ስራ፣መርሳ ከተማ ስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት የመንገድ ጥገና ግንባታ ስራ ዝቅተኛ ዋጋ ከአቀረበው ተጫራች መፈፀም ሲገባው ያለምንም አሳማኝ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበው አቅራቢ የተፈፀመ የግንባታ ስራ እንዲሁም በብልጫ የተከፈለ ደመወዝና ውሎ አበል፣
- **ጉባላፍቱ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 342,389.60 ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በተመሳሳይ ቀናት በድጋሚ፣ መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ እና ከታሪፍ በላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ወልዲያ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር** 330,996.95 ለላቦራቶሪ ክፍል አገልግሎት የሚውል ሪኤጀንቶች በውስን ጨረታ ግዥ ሲፈጽም በጥቅል ወይም በሎት ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ እያለ ከከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበ አቅራቢ ያለምንም አሳማኝ ምክንያት ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣ ሆስፒታሉ የላውደሪ አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ሰራተኞች በተለያዩ ወራት ክፍያ ሲፈጽም ጨረታ ተወዳድረው ካሸነፉት በላይ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፣ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ወይም ለቆዩበት ውሎ አበል ተከፍሎ እያለ በተመሳሳይ ቀን በድጋሚ የተከፈለ፣ለማህበረሰብ አቀፍ መድሃኒት ቤት አገልግሎት መስጫ ለተከራየው ቤት ኪራይ ሲፈፅም በውሉ መሰረት መፈፀም ሲገባው ከውሉ በላይ በየወሩ አስር ፐርሰንት እየተጨመረ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 325,652.85 ከ15-18/11/2011 ዓ/ም ድረስ የወረዳው ባለሙያዎች መስክ ለወጡበት ውሎ አበል ሲከፈል በብልጫ እና በተመሳሳይ ቀናት ከተለያዩ የሂሳብ ፕሮጀክቶች በድጋሚ የተከፈለ የውሎ አበል፣የቱቻ 2ና ደረጃ ት/ቤት ሁለት የሳይንስ ብሎክ ግንባታ ተከናውኖ የመጨረሻ ዙር ክፍያ እና የላበራቶሪ ብሎክ አንድ

ክፍያ ለተሰራበት ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣የእንስሳት ሀብት ተጠሪ ጽ/ቤት ሰራተኞች የታህሳስ ወር ደመወዝ ሲከፈል በብልጫ ጸድቆ የተፈፀመ ክፍያ፣በሰሌዳ ቁጥር 4-02138 እና 4-02549 ተሽከርካሪዎች መስክ ሳይወጡ እንደወጡ በማስመሰል የተለያየ የነዳጅ ደረሰኝ በማቅረብ የተወራረደ ነዳጅ፣ለተለያዩ ሰራተኞች መስክ የወጡበት ውሎ አበል ሲከፈል ከመስክ ቆይታ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣

- **ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 315,480.00 መስክ ለስራ ሳይወጣ የተከፈለ ውሎ አበል፣ለኪነት ቡድን አባላት ለሚሰሯቸው ስራዎች የአገልግሎት ክፍያ እየተከፈላቸው እንዲደገፉ የአገልግሎት ውል የፈፀሙ ሲሆን ይህን በመተላለፍ የኮንትራት ቅጥር ውሳኔ በማሳለፍ አላግባብ የተከፈለ የደመወዝ ሂሳብ፣
- **ግዳን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 284,181.00 ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በተመሳሳ ቀናት በድጋሜ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ቡግና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 213,148.19 ሰራተኞች መስክ ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ፣ መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ እና ከታሪፍ በላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከልብር** 164,278.19 ከውሎ አበል መክፈያ ታሪፈ በላይ፣ መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ፣በድጋሜ በተመሳሳይ ቀናት የተከፈለ የውሎ አበል፣ስልጠና ላይ ሳይሳተፉ እንደሳተፉ ተደርጎ የተከፈለ ሂሳብ፣መስክ ከቆዩበት ቀናት በላይ የተከፈለ ውሎ አበል፣ የኤክስካባተር ኪራይ ክፍያ ሲፈፀም ጨረታውን ከአሸነፈው ድርጅት ከአቀረበው ዋጋ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣ ተሽከርካሪዋ ከተፈቀደላት ኖርማላይዜሽን በላይ አላግባብ የተከፈለ የነዳጅ ወጪ፣የወረዳው ሰራተኞች ደረጃ እድገት ሲያድጉ በብልጫ የከፈለ የደመወዝ ሂሳብ፣
- **ሰቆጣ ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 162,167.91 በሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጽ/ቤት በየቀበሌው ተመድበው እየሰሩ ላሉ ፖሊሶች ደመወዛቸው አነስተኛ በመሆኑ ለቤት ከራይ እና ለኑሮ ውድነት እንዲያግዝ በሚል በቀን 07/04/2012 ዓ/ም በከንቲባ ጽ/ቤት ከፍተኛ አመራር ተወስኖ የሰራተኞችን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም መመሪያ በጣሰ መልኩ አላግባብ የተከፈለ፣ ከሰቆጣ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት መደበኛ በጀት ላይ የምክር ቤቱ ጽ/ቤት አዳራሽ ግንባታ ለአከናወነው የስራ ተቋራጭ 1ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣
- **አብክመ ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ብር** 151,942.91 ስልጠና ላይ ሳይሳተፉ እንደተሳተፉ ተደርጎ የተከፈለ የስልጠና አበል፣በእንጅባራ ከተማ የሚገኘው የኢመርጀንሲ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ላልተሰራ ስራ ለተቋራጩ የተከፈለ ክፍያ፣

- ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 82,275.15 በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል እና መስክ ባልተሄደበት ቦታ ደረሰኝ በማቅረብ በድጋሜ የተወራረደ የነዳጅ ሂሳብ፣

የ2012 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2011 በጀት ዓመት ብር 5,678,736.69 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ17 በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 6,765,107.94 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየተባባሰ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 264,634.41(2.13%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ብር 12,179,210.22 ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 23/2012 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

1.12. የግንባታ ስራዎች ወጪ የኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

- ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ22(7.31%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,546,545.04 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከብር 400,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- የአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ልዩ ኦዲት በባህር ዳር ከተማ ለአድማ ብተና ፖሊሶች ካምፕ፣ ለሻዎር እና ለሽንት ቤት ግንባታ ለተገናወነበት ክፍያ ሲፈፀም የተሰራውን ስራ የሚያሳይ የስራ ስፍር ልኬት እና የስራ ዝርዝር እንዲሁም የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ በግምት ይህን ያህል ፐርሰንት ተከናውኗል በሚል የተፈጸመ ክፍያ ብር 6,337,075.74፣
- አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ቻናል-2 ሂሳብ በቡግና ወረዳ አይና ጤና ጣቢያ የአይን ቀዶ ህክምና ክፍል ግንባታ፣በጃናሞራ ወረዳ የአሰንጋ ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ፣በባንጃ ወረዳ ከሳ ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ እና በአልቡኮ ወረዳ በሳልመኒ ጤና ጣቢያ የቀዶ ህክምና ግንባታ ለተከናወነበት የተለያዩ ዙሮች ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት(Take off sheet) ሳያዘጋጅለት የተገኘ የግንባታ ወጪ እንዲሁም በሰከላ ወረዳ የአጉት ጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ፣በመተማ ካላዛር ሆስፒታል እና በእብናት ወረዳ የቀራኒዎ ጤና ጣቢያ ግንባታ ስራ ያከናወኑ የስራ ተቋራጩች ስራውን በሚያቋርጡበት ጊዜ የግንባታ ማቋረጫ ሰነድ በሚዘጋጅበት ወቅት የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይዘጋጅ የተቋረጠ የግንባታ ሂሳብ ብር 3,547,461.59፣
- ደንበጫ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ሲከናወን 1ኛ ፣2ኛ እና የመጨረሻ ዙር፣የአስተዳደር ጽ/ቤት የዲች ቦይ ግንባታ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና የመጨረሻ ዙር፣በአገልግሎት ጽ/ቤት የአዳራሽ ማስፋፊያ ግንባታ

ሲከናወን የ2ኛ ዙር፣ወደ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የሚወስደው መንገድ የኮብል ንጣፍ ስራ 2ኛ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ሂሳብ ብር 3,051,773.83፣

- ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ በቀበሌ 16 ለየልዩ ሐይል ፖሊስ መኖሪያ ካምፕ ፣ የሽንት ቤት እና የሻዎር ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈጸም የስራ ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 2,377,566.06፣
- ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት በተለያዩ ቀበሌዎች የሸድ ግንባታ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ዙር፤በትምህርት ጽ/ቤት በተለያዩ ቀበሌዎች የትምህርት ቤት ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዙር የስራ ስፍር ልኬታ ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 2,155,962.26፣
- ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ግብርና ጽ/ቤት በሴፍትኔት በጀት ለሲትር ቀበሌ የመስኖ ካናል የሪቴንግ ዎል ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዙር የስራ ስፍር ልኬታ ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 966,276.14፣
- ወረኢሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የወረዳው ውሃ ኢነርጅ ጽ/ቤት በ014 ቀበሌ ላይ ልዩ ቦታው የውል በተባለው አካባቢ ለሚያስገነባው የመጠጥ ውሃ ግንባታ የ2ኛ፣የ3ኛ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ፤የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ለሚያስገነባው የኮንተብ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የመማሪያ ክፍል የመጀመሪያ ዙር እና አስተዳደር ጽ/ቤት የሚያስገነባው የአጥር ግንባታ የመጨረሻ ዙር፤ የወረዳው ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት በ01 ቀበሌ ሰኞ ገበያ ለሚያስገነባው የሸድ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ፣ የወረዳው መንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ሰኞ ቦሎ መንገድ እና ሰኞ ገበያ የመነሃሪያ የመጸዳጃ ቤት እና የአጥር ግንባታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዙር እንዲሁም የወረዳው አንስሳት ሃብት ልማት ጽ/ቤት በ012 ቀበሌ ለሚያስገነባው የእንስሳት ክሊኒክ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ዝርዝርና የስራ ስፍር ልኬታ ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ
ብር 740,556.44፣
- አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለሻውራ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ስራ ክፍያ ሲፈጸም የስራ ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍ ብር 710,526.43፣
- ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የወረዳው ቴክኒክና ሙያ ልማት ጽ/ቤት አዲሱ ገበያ አካባቢ ለሚያስገነበው የሸድ እና ውሀ ልክ ግንባታ የ2ኛ ዙር ክፍያ ፣ቁንድማሪ አካባቢ ለሚያስገነባው የሸድ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ እና የመጨረሻ ክፍያ፣ ደገር መናሃሪያ አካባቢ ለሚያስገነባው የሸድና ውሃ ልክ ግንባታ የ1ኛ ዙር ክፍያ፣አቤት ውሃ አካባቢ ለሚያስገነባው የሸድ ውሃ ግንባታ የ1ኛ ዙር ክፍያ እንዲሁም አቤት ውሃ አሮጌው ገበያ

አካባቢ ለሚያስገነበው የሸድ ውሃ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬታ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 617,220.32 ናቸው፡፡

ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት/የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል በስራ ዝርዝሩ እና ውለታው መሰረት ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ የተተካ ወይም ተገቢው ማስረጃ የቀረበለት ሂሳብ ስለመኖሩ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

1.13.ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪን በተመለከተ፤

- ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ21 (6.98%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 10,253,842.42 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡

- በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 10,571,713.53 ጋር ሲነፃፀር በ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ4 እና በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 317,871.11 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ መ/ቤቶች ችግሮቻቸው እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ቢያመላክትም፡፡
    - የአብክመ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ብር 3,486,309.52 እና የደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,122,004.18 በመያዝ በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ችግሩ ገዝፎ የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት ብር 658,051.50 ከኦዲት በኂላ ማስረጃ የቀረበለት ስለመሆኑ በግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 9,595,790.92 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

1.14.ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች በተመለከተ፤

- ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ5(1.66%) መ/ቤቶች ብር 3,891,232.15 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር ተረጋግጦ በግብረ መልስ እንዲገለጽ ብናሳስብም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/20132 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

ከፍተኛ ወጪ ይዘው ማስረጃ ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም ከብር 500,000 በላይ የያዙ መ/ቤቶች፡-

- ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,723,725.41፣ደቡብ አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስማዕከል ብር 768,300.00፣ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 744,378.04፣ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 595,189.37 የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ስለሆነም ማስረጃዎቹ ተገቢ ክፍያ እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

1.15. የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

- የዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና የዋጋ ቅናሽ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ60(19.93%) መ/ቤቶች በር 58,672,985.26 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ አፈፃፀም ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝቷል፡፡

የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው ከብር 1,100,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ልዩ ኦዲት ብር 12,674,151.42 ኮሚሽኑ በባህር ዳር ከተማ አድማ ብተና የፖሊስ ካምፕ፣ሻወር እና ሽንት ቤት ግንባታ ለማከናወን ከሶስት የስራ ተቋራጮች ጋር የውል ስምምነት ሲፈጽም የውል ስምምነቱ በሚመለከተው የፍትህ አካል ተመርምሮ ሳይፀድቅ የተፈፀመ የግንባታ ግዥ
- ዳውንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 9,361,757.83 የግዥ መጠየቂያ ያልቀረበለት የነዳጅ ግዥ፣ የግንባታ ማቴሪያል ግዥ ሲፈጸም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት የተፈጸመ ግዥ፣ አስተዳደር

ጽ/ቤት ለሚያስገነበው ግንባታ ግዥ ሲፈጸም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራጭ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣የተቋረራጭ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፣የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር አቅርበው ሳለ የንግድ ፈቃድ የምስክር ወረቅ የለውም በማለት ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራጭ እንዲያሸንፍ ተደርጎ የተፈፀመ ግዥ፣

- ፈለገ ህይዎት አጠቃላይ እስፔሻላዝድ ሆስፒታል ብር 4,466,402.01 የተለያዩ የህትመት አገልግሎቶች ግዥ ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይቀርብ በቀጥታ፣በውስን ጨረታ እና በፕሩፎርማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ደምበጫ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,237,158.38 ለከተማ አገልግሎት የሚውል የአገለገለ ኤክስካቫተር ማሽን ግዥ ሲፈጸም በባለሙያ እስፔሲፊኬሽን ሳይዘጋጅ የተፈፀመ ግዥ፣ ለፖሊስ አገልግሎት የሚውል የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃ እና የአዳራሽ ኪራይ አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ
- ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,921,062.73 የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑ፣የመለዋወጫ እቃዎች፣የተሽከርካሪ የእግር ሰረቪስ፣የውሃ እቃዎች ግዥ፣ካቦ ባለ100 ሜትር እና ኤሌክትሪካል ዋዮር፣የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና የስሚቶ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እንዲሁም የነዳጅ ግዥ፣የተሽከርካሪ ጥገና ፣የመድሃኒት ግዥ ሲፈፀም የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብለት የተፈፀመ ግዥ፣
- ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,908,675.70 ለግብርና ጽ/ቤት የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያዎች እና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ ከመፈፀሙ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ግዥ፣
- አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ቻናል-2 ሂሳብ ብር 1,716,002.98 የላፕ ቶፕ ኮምፒውተር ግዥ ለመፈፀም ቢሮው ባወጣው ግልጽ ጨረታ መሰረት አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ጋር የተያዘ የውል ስምምነት በፍትህ አካላት ተመርምሮ ሳይጸድቅ የተያዘ የውል ስምምነት እና የተሽከርካሪ የጥገና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይቀርብ በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል 1,629,288.80 ለሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል የፕላንት ማሽነሪ ግዥ ሲፈፀም ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ግዥ፣
- መንዝ ላሎ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,415,736.84 ለሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል የመኪና መለዋወጫ ግዥ ሲፈጸም ለቀጥታ ግዥ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያለ ግልጽ ጨረታ በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እና የመኪና መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም የግዥ መጠዩቂያና ማዘዣ ያልቀረበለት ግዥ፣

- አብክመ አመራር አካዳሚ ብር 1,384,226.75 የመኪና መለዋወጫ፣የጀኔሬተር ባትሪ ፣የፍራፍሬ ፣ አላቂ የጽዳት ዕቃዎች እና ቆርቆሮ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ፣በውስን እና በፐሩፎርማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ኮምቦልቻ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 1,336,583.28 የተለያዩ ለትምህርት የሚያገለግሉ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፀም የውል ስምምነቱ በሚመለከተው ፍትህ አካል ተመርምሮ ሳፀድቅ የተፈፀመ ግዥ፣
- ቡሬ ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 1,325,820.22 የውሃ ፓምፕ ጀኔሬተር እና የውሃ ቆጣሪ ግዥ ሲፈጸም በተጠየቀው እስፔሲፊኬሽን መሰረት ጥራቱን ጠብቆ ስለመገዛቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እና የቧንቧ መገጣጠሚያ ግዥ ሲፈጸም የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ የተፈጸመ ግዥ፣ ዋና ዋናዎቹና የግዥ አፈፃፀምን ያልተከተለ ግዥዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

- ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ መመሪያውን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች ባሳሰብነው መሰረት ለብር 280,652.78 ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ከተገኘው ግብረ መልስ መረዳት የተቻለ ሲሆን በቀሪው ብር 58,392,332.48 ላይ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2012 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡
- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2011 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 29,254,400.10 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ16 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 29,418,585.16 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል አፈፃፀማቸው የተሻለ እንዳልሆነ ያመላክታል፡፡

1.16.የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

1.16.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ:-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ108 መ/ቤቶች ብር 1,030,777,107.72 የተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡
- በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት ተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 1,114,129,856.19 ጋር ሲነፃፀር በ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ11 የጨመረ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 83,352,748.47 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች እየቀነሰ መሄዱን ያመለክታል፡፡

- በወቅቱ ያልተከፈለ ከብር 20 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል፡-
    - ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 132,165,233.00 ፣ ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ብር 125,017,733.22 ፣ ደሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 75,080,792.67፣ደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 58,978,515.34 ፣ አብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ብር 53,368,773.99 ፣ ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 49,797,365.54 ፣ ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 43,421,570.19 ፣ ጎንደር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 41,906,956.08፣ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 38,495,853.01 ፣ ስራ አመራር አካዳሚ ብር 29,610,986.75 ፣ ሰሜን ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 28,852,873.84፣ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 25,169,197.73 ፣ ዋግኸምራ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 21,211,043.41 ፣ የተከፋይ ዕዳ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ጊዜ ስላላቸው በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ባሳሰብነው መሰረት ብር 268,000.00 ከኦዲት በኂላ ለባለጥቅሙ የተከፈለ ወይም ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው ብር 1,030,509,107.72 ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

1.17. ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ፤

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገላቸው መ/ቤቶች መካከል በ26 መ/ቤቶች ብር 38,260,838.33 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቸ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ በግብረ መልስ ስላልተገለፀ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

1.18. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት በተመለከተ፤

- የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሂሳብ ለኦዲት ስራ ዝግጁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 227 መ/ቤቶች መካከል በ73 (32.16%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ የሚያስችል አሰራር ሳይኖር ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር መሰረታዊ ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይኖር ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ በየመ/ቤቱ እንዲተገበርና እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

1.18.1 የንብረት ሂሳብ ጉድለትን በተመለከተ፡-

1 በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በልዩ ኦዲት አሰራር ኦዲት በተደረገ 2 መ/ቤቶች በጉድለት ብር 217,783.05 መገኘቱ፤

- **የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ብር 137,491.75** ለትምህርት ቤቶች ለማሰራጨት የንብረት ክፍል ሰራተኛ የተረከቡት እና ወጭ ያደረጉት ላፕ ቶፕ ኮምፒውተር ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት፣
- **በዋና ኦዲተር መ/ቤት የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት** ተወካይ ንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ከ01/5/2011-04/13/2011 ዓ.ም እና ከ25/12/2009-04/13/2011 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በምላሹ አልተገለፀልንም፡፡

ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት ሪፖርት በተመለከተ

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን መደበኛ ኦዲት በተደረጉ 227 መ/ቤቶች በተደረገው የክትትል ኦዲት የ2011 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ35 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 23/2013 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ዝርዝሩም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- አንጎት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 94,000.00፣ ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የእንስሳት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብር 34,579.00፣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 135,613.00 እና በብልጫ የተፈፀመ ወጭ ብር 59,416.15፣ለኦዲት ያልቀረበ የወጭ ማስረጃ ብር 4,828,817.11፣
- ወልድያ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 21,295.30፣
- ግዳን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 21,736.35፣
- ጉባላፍቶ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከቅድሚያ ክፍያ ያልተቀነሰ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 77,477.90 እና ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 389,342.18፣
- ላሊበላ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ለኦዲት ተፈልጎ ያልቀረበ የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኝ

  ብር 120,495.55፣
- ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በብልጫ የተከፈለ ክፍያ ብር 100,290.63፣ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 116,844.90፣
- ጋዞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግብባ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 19,722.00፣
- ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 19,322.00፣
- ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 15,850.00፣
- አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 76,249.00፣ለኦዲት ያልቀረበ የስፖርት ገቢ መሰብሰቢ ደረሰኝ ብር 164,896.00፣ ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 16,601.88፣

- ሀይቅ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ
  ብር 216,049.33፣
- መሀል ሳንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ብር 30,750.00፣
- ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 15,523.10፣ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 257,698.78፣በብልጫ የተከፈለ ወጭ ብር 17,080.78፣የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 107,094.59፣
- ደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 17,133.94፣አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 46,049.65፣
- መቅደላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 46,049.65 እና ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 20,650.77፣
- ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 338,964.89፣የግንባታ ስፍር ልኬት ወረቀት ያልቀረበት ወጭ ብር 478,486.24፣ በብልጫ የፀደቀ ወጭ ብር 43,886.99፣
- ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 114,294.00፣ በብልጫ የተከፈለ ወጭ ብር 13,717.65፣ለኦዲት ስራ ያልቀረበ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 279,090.77፣የግንባታ የስራ ስፍር ወረቀት ያልቀረበለት ወጭ ብር 512,723.10፣
- ዳዋ ጨፋ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 19,505.50፣
- ባቲ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 124,566.00፣በብልጫ ፀድቆ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 70,814.24፣
- ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ 13,106.25፣
- ሸዋ ሮቢት ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል
  ብር 17,234.00፣
- ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈጸመ ክፍያ
  ብር 21,900.00
- ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ለኦዲት ያልቀረበ የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኝ

ብር 153,836.56፣

- ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በብልጫ የተከፈለ ወጭ ብር 20,193.21፣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 14,584.00፣
- ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለኦዲት ያልቀረበ የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኝ ብር 33,525.00፣
- ደቡብ አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ያለማስረጃ የተፈፀመ ወጭ ብር 20,900.00፣
- ደብረ ማርቆስ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ለኦዲት ያልቀረበ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 18,130.00፣
- ስናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 14,723.92፣
- ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በብልጫ የተከፈለ የግባታ ክፍያ ብር 143,068.81፣

እነዚህ በእያንዳንዱ የግኝት ርዕስ ከብር 10,000.00 በላይ የሆኑ በ28 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ የሚሰራ ይሆናል፡፡

- በተለይም አላግባብ/በብልጫ/ላልተሰራ ስራ የተከፈሉ ውሎ አበል እና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 1,033,907.24 ከሚመለከታቸው አካላት ላይ መተካት ሲገባው ይህ አለመፈፀሙ የተጠያቂነት አሰራሩ የላላ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ጉዳዩን መከታተል እና የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው አካላት በህግ ሊጠየቁ ይገባል፡፡
- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ በድምሩ ብር 635,181.67 በተመለከተ ህጋዊ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው ይህ አለመፈጸሙ በገቢ ላይ ተመስርቶ በግብር ከፋዩ ላይ የሚጣልን ግብርና ታክስ ለመሰወር እድል የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ የክፍያውን ተዓማኒነት አጠራጣሪ ስለሚያደርገው ተገቢው እርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- ለኦዲት ስራ ሳይቀርቡ እና በውስጥ ኦዲተር ሳይረጋገጡ የቀሩ ወጭ የተፈፀመባቸው የወጭ ማስረጃዎች ብር 4,828,817.11 እና የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈፀመ ወጭ ብር 991,209.34 ላይ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱ የሚያስጠይቅ እና

ተግባሩም ለሌሎች ተቋማትም መልካም ያልሆነ አርዓያ ሆኖ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመ ባለመታወቁ ከፍተኛ ስጋት የሚያሳድር በመሆኑ ተከታትለው ተገቢ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ በነበረባቸው አካላት ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

1.21. የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን በተመለከተ፤

1.21.1 የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 301 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት ከተሰጠባቸው 218 መ/ቤቶች ውስጥ ለ36(12%) ንፁህ፣ለ157 (52%) ከዚህ በስተቀር፣ለ25(4%) አጥጋቢ አይደለም የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን "አጥጋቢ አይደለም" የሚለው የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች አነስተኛ በመሆናቸው አብዛኛው የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አድርገው በጀትን ለመምራት ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

1.21.2 የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ ተቋማት በመልስ አሰጣጥ ረገድ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ይህም የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡

1.21.3 የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ በሚመለከት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 9,198,998.71 የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 6,626,874.62 ከቀድሞው ገንዘብ ያዦች በጉድለት የተገኘ ነው፡፡በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ10 መ/ቤት ብር 3,504,098.41 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ7 መ/ቤት የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 10,782,121.14 የተገኘ ነው፡፡በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም ላይ በ24 መ/ቤቶች ያለው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጭ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

1.21.4 የገቢ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ በ5 መ/ቤቶች ብር 2,348,398.76 የማጭበርበር ድርጊት ተፈጽሞ ለግል ጥቅም ውሎ የተገኘ፣በ2 መ/ቤቶች ብር 463,583.59 የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይሰበሰብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ፣ በ107 መ/ቤቶች ብር 295,183,360.47 ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ የተገኘ ሲሆን ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ43 መ/ቤቶች ብር 298,798,705.02 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፣

1.21.5 የተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ115 መ/ቤቶች ብር 3,939,749,122.20 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡በ16 መ/ቤቶች የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 65,591,055.76 መገኘቱ፣በ32 መ/ቤቶች ብር 84,501,064.06 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

1.21.6 የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፡-

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ21 መ/ቤቶች ብር 11,118,146.21 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ፣በ11 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,379,361.49 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተገኘ፣ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ106 መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ፣አላግባብ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 12,443,844.63 አላግባብ ተፈጽሞ የተገኘ፣ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ22 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,546,545.04 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ፣ማንኛውም ክፍያ በወጭ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ21 መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና

አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 10,253,842.41 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና ተመዝግቦ የተገኘ፣ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ5 መ/ቤቶች ብር 3,891,232.15 ስለ ክፍያው ትክክለኛነት የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ፣የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ60 መ/ቤቶች ብር 58,672,985.26 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

1.21.7 የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት፡-

- የ2012 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ108 መ/ቤቶች ብር 1,030,777,107.72 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይከፈል ወይም ወደ ተጣራ ሀብት ሳይቀየር የተገኘ ሲሆን በ26 መ/ቤቶች ብር 38,260,838.33 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

1.21.8 የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

- በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 227 መ/ቤቶች መካከል በ73(32.16%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

1.22. የማሻሻያ አስተያየት በተመለከተ፤

- በ2012 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

1.22.1 በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ፤

በኦዲት ስራው ከተስተዋሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአንዳንድ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ እና ኦዲት በሚደረጉ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተከሰተ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ እየተዳረገ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

1.22.2 የገቢ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

በገቢ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ መሰብሰብ እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

1.22.3 የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

1.22.4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር ስለማስፈለጉ

በኦዲት ውጤቱ መሰረት መረዳት እንደተቻለው በበርካታ መ/ቤቶች ተሰብሳቢ ሂሳቡ መቼ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩን የሚያሳውቅ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር እየተዘጋጀ ባለመሆኑ ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት ይገባል፡፡

1.22.5 የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤

- በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ የሚገባ ሲሆን ይህን ተግባራዊ በማያደርጉ የየተቋሙ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ስራን ባልተመቸ ሁኔታ መምራትና ለብክነት በር በመክፈት ድርጊት ሊጠየቁ ይገባል፡፡

1.22.6 የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር እንደሚገባው፡፡

- ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፤ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ

በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሜቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት መቋቋም ይችል ዘንድ ከፌደራልና ከሌሎች አቻ ክልሎች የተወሰደው ልምድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጪ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ዋና ኦዲተሯ የምክር ቤት አባላትን፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎችን፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎችን፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን በሥራ ሂደት ላደረጉት የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና አቅርበው ሪፖርታቸውን ያጠቃለሉ ሲሆን ሪፖርቱም በወቅቱ በተገኙት የምክርቤት አባላት በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

የሺመቤት ደምሴ(ዶ/ር)

ዋና ኦዲተር

ሰኔ 2013 ዓ.ም

ባህርዳር